# ቀ ማ ዮ ች

አጭር ልቦለድ
ዓለማየሁ ታዬ
alalemayehu@yahoo.com

ጽልመት አልነገሰም

ደብዛዛ ጨረቃ ሰማዩ ላይ አትሽከረመምም

ከዋክብት ፈንጠቅ ጠቅ ጠቅ አላሉም-ጀንበር ግን ጠልቃለች

ጀንበር ከጠለቀችበት አጥናፍ ፊት ለፊት አነስተኛይቱ ዱብ እቁንጮዋ ላይ

ባለ ቁረንጮዎች ይዛለች፡ - ሌምጥና ጠብደሉ

እሷ በትቷም

አፍንጫጎራዳ

ከናፍረ ወፍራም

የደረሰች ኮረዳ

እሳቸው ኮሳሳ

በጠብደልነታቸው ዘመን

መቶ ከሎ ጤፍ ተሸክመው ዳገት የሚሮጡ

አሁን ግን ዕድሜ ካቲካላ ያኮሰማናቸው ለማኝ ባለ ቁርንጮ፡

ሁለቱ- ጀንበር ከመጥለቋ በፊት የጀመሩ አሁንም ከበትቷቸው

ቅሚል ቅጫም ይቀምሳሉ፡፡

ዝም ብለዋል ወሬ አልቆባቸዋል፡፡ ፊት ለፊታቸው ቀጭን አስፋልት መንገድ አለ፡ -

መንገዱን እየሰለሉ

ይቀምሳሉ፡፡ መንገዱ ጭር ሲል የሌምጥ ቀሚስ ከፊት ፊት ፊት ይላል

ወፍራም ቀይ ባቶቿ ይጋለጣሉ

ብልጣ ብልጥ አይኖቿ ይፈዛሉ

ፊትዋ ይበራል-ከናፍርዋን ቶሎ ቶሎ እየላሰች በላይ በላዩ ስትተነፍስ

ትንፋሽዋ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ከርቀት ይሰማል፡፡

ድንገት የተቃቀፉ ወይ የተዘጋጉ

የሚያሽካኩ አለያም ሃሳብ የሚያኙኩ

ሰዎች ብቅ ሲሉ

ት . ሠ. በ. ሠ. ባ . ለች

ትንፋሽዋ እየረገበ ይመጣል

የጨቀየ ቀይ ቀለም የተንጠበጠበባቸው አወራና አወራ

ጣቶቿ ስራቸውን ይጀምራሉ፡፡

እሳቸው ያደፈች የተቀዳደደች ቡላ ኮፊያ እግንባራቸው ላይ ልጥፍ ብለለች፡፡

የግራ ቅንደባቸው አይታይም፡፡ አጭር ጉንጫ ም ፊታቸው በጢ ም ተወሯል፡- አይኖቻቸው ጀንበር ስታጣበረብራቸው ቢጨ ናበሱም አሁን ግን ጎላ ጎላ ብለዋል፡፡ የሚቋምጡትን ቡትቶ ቦላሌ አወልቀው ጉያቸውን ሸፍው በታል፡፡

ረጋ ያለው ሰላማዊ ነፋስ ሱሪያቸውን ይገልበውና አንዳንዴ ይጋለጣሉ፡፡ ያኔ ዐይናቸውን ሌምጥ ላይ ያፈጣሉ፡፡ መ ጓጎል ያሳበጠው የግራ አወራ ጣታቸውን ነከስ ነከስ ያደርጉታል፡፡ ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ ከርቀት ይሰማል፡፡

ሌምጥ አጭር ቁርንጫጭ ፀጉሯን ንፋስ ወደ ግራ ያስተኛውና ልትመልሰው ዘወር ስትል

ይ. ሠ. በ. ሠ. ባ. ሉ

አይኖቻቸው ይታጠፉሉ

ትንፋሻቸው ይረግባል

የጨቀየ ቀይ ቀለም የተቀቡ አወራና ሌባ ጣታቸው ስራ ይጀምራሉ፡፡

የተቀመ ጡ በት ቂጣቸውን ይቆረቁረወና ወደ ኋላ ሸርተት ይላሉ፡፡ ከዳቡ በስተወዲህ አጥር አለ፡፡ አጥሩ ስር ዐይነ ምድር የጥቁር አፈር ሽታ ተቀላቅሎበት አፍንጫ ን በልዝቡ ይወጋል እዚህ ግን ያስነጠሰ የለም፡፡

ጨለም ለም ለም ለም እያለ

ከዋክብት ፈንጠቅ ጠ ቅ ጠ ቅ ሲሉ

ጨረቃ ሰለም ለም ለም ትላለች

አሁንም ቀሚዎቹ ይቀምላሉ፡፡ በጣም ተጠጋግተዋል፡፡ የሌምጥ ጉርድ ቀሚ ስ እንደባቷ ቀይ ነው፡፡ አሁን ግን በምሽቱ ጥላ መጠየም ጀምሯል፡፡ ተጋልጧ ል ጭኗ ከፉኛ ተጋልጧ ል፡

የጠበደሎ አይኖቻቸው እንጂ እጆቻቸው አልደረሱባትም፡፡ ድንገት የተጠሩ ይመስል እሳቸው አይኖቻቸውን ከዳቡ ባሻገር አሻገሩ፡፡

ጩፊቃ የፈዘዘ አይኖቿን ታስለመልማለች

ከዋክብት አደፍጠዋል

የባህር ማዶ ዛፎች ከንፋሱ ጋር ተቃቅፈው እስክስታ ይወርዳሉ

" አሁ. / "

" አሁ. / " ሌምጥ ደረቷን ይዛ አሳለች

" ይምርሽ / " አሉና ደረቷን ደገፏት አራት እጆች

ተያያዙ- አራት እጆች ስራ በዛባቸው፡ -

"ጠ ./

ረ. /

ረ./

ረር./ "

የሌምጥ ቀሚስ ሲቀደድ ማንም አልሰማም፡፡ ጨረቃ ብቻ ነገሩ አሳፍሯት ቶሎ ብላ ከባድ ደመና ወስጥ ተሸሸገች፡፡

አንድ አይኗንም በሰያፍ አጮለገች፡፡

"እረ ምን አስቸኮሎት./ ምን አስቸኮሎት./" ሌምጥ ቃተተች

ከዋክብት እንዳደፈጡ ሆነው በሹክሹክታ አሽሟጠጡ፡

ነፋሱ ግን የሚሰራውን አሳጣው የዛፎቹን ቅጠላት ጮቤ አስረገጣቸው፡.....